# የማጋፊር ፖለቲካ

**ዮናስ 12-18-14**

በየአገሩ የሚካሄዱ ምርጫዎች አብዛኛውን ጊዜ በሶስት ምዕራፎች ተከፍለው ይካሄዳሉ፡፡ በሶስቱም ምዕራፎች ህብረተሰቡና ተፎካካሪ ፓርቲዎች የየራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ የመጀመሪያው ተቀባይነት ለማግኘት በሰፊው የምረጡኝ ዘመቻ ላይ የተመሰረተ ፉክክርና ትግል የሚካሄድበት ምዕራፍ ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ በተለምዶ ቅድመ ምርጫ ተብሎ ይወሰዳል፡፡ የተለያዩ ፓርቲዎች የሚያርምዷቸው አማራጮች በመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሰርዓት ውስጥ በቅድመ ምርጫ ሂደቱ ተፎካካሪ ሆነው ለህዝቡ በነጻነት ይቀርባሉ፡፡ ፓርቲዎቹ ወይም እጩ ተፎካካሪዎች ህዝብ በሚገኝበት በሁሉም ቦታ ተገኝተው በነጻነት ይቀሰቅሳሉ ፡፡ በመገናኛ ብዙሃን በቂ እድል አግኝተው አማራጫቸውን ለህዝብ ያሳውቃሉ፡፡ ህዝቡም ከቀረቡለት አማራጮች መካከል የሚበጀውን ለመምረጥ የአቋሞች ፍተሻ ያደርጋል፡፡ በአጭሩ  የአንድ ምርጫ ዲሞክራሲያዊ መሆን አለመሆን የሚለካበት የመጀመሪያውና ትክክለኛው ወቅት ይህ ነው፡፡

ከምርጫ አኳያ ሶስተኛው ምዕራፍ ድህረ ምርጫ ተብሎ የሚታወቀውና የምርጫውን ሂደት ከመወሰን አኳያ ትርጉም ያለው ፋይዳ የሌለው ወቅት ቢሆንም በቆጠራው ውጤት ላይ በመመስረት አሸናፊው ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች የሚታወጁበትና በውጤቱ መሰረት መንግስት የመመሰርት ሃላፊነት የሚረከቡበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ተፎካካሪ ፓርቲዎች በተገኘው ውጤት መሰረት አቋማቸውን ይገልጻሉ፡፡ የዴሞክራሲ ባህላቸው ያደገና ሽንፈታቸውን በፀጋ ለመቀበል ዝግጁ የሆኑት መሸነፋቸውን አምናው ለአሸናፊው ወገን የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡በሌላ በኩል በምርጫው ሂደትና በቆጠራው ወቅት ችግር ተፈጥሯል ካሉ ደግሞ በአገሩ ህግ መሰረት የማጣራት ሥራ ተካሂዶ ችግሩ ህጋዊ እልባት እንዲያገኝ የመጠየቅ መብታቸው የሚጠበቅበት አግባብ ነው፡፡

በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ከላይ የተመለከተ ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔም ሆነ ተግባራዊ መርሆ በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ

ስለዴሞክራሲ ሥርዓት እተጋለሁ ከሚሉ የፖለቲካ ፓርተዎች ሁሉ የሚጠበቅና የግድ የሚል ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን ስለ ዴሞክራሲ በነቢብ ከሚያነበንቡት የሃገሬ ተቃዋሚዎች የበዙና ስለ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከላይ በተመለከተ መርሆ ተመርተውና በአማራጭ ሃሳቦች ታግዘው ብዙ አበርክቶ ብንጠብቃቸውም ይኸው ላለፉት 10 ዓመታት በተለየ ፖለቲካን በማጋፈር ተጠምደው የመገኘታቸው ነገር የሚያሳዝንም የሚያሳስብም ሆኗል፡፡

በመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በውስጥም በውጭም የተከበሩና ሁሉንም የሚገዙ ናቸው፡፡ የህግ የበላይነትና ህገ መንግስቱን መሠረት አድርገው የሚወጡ ህጎች ሁሉ በፓርቲዎች ይጠበቃሉ እንጂ አይደፈሩም፡፡ የፓርቲዎች መለያና መታወቂያ ለህዝቡ የሚያቀርቧቸው አማራጭ ፕሮግራሞች እንጂ የገገር ሥርዓቱ ድክመቶች አይደሉም፡፡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆ መሠረት የበላይነት የሚኖረው ሃሳብ እንጂ ጉልበትና ፍጥጫ፣ አልያም ቡድንተኝነት አይደለም፡፡ የፓርቲ ዲሲፕሊን ውስጠ ዲሞክራሲያዊ ፍጭት ደግሞ ስለ ሃሳብ የበላይነትም ሆነ ለሂደቱ መጠናከር ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በየነገሩ ሁሉ ላይ መነዛነዝና ማላዘን ከአማራጭ ይልቅ የማጋፈር መግለጫን ሥራ ማድረግ መጀመሪያ የሚጎዳው በዚህ የሚገለጹትን ፓርቲዎች ነው፡፡ቀጥሎም አማራጭ የሚሻውን ህዝብና ገገር ሥርዓቱን ነው፡፡

በተለይ ባለፉት 10 ዓመታት ወይም ከምርጫ 97 ዋዜማ ጀምሮ በሃገሬ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የያዙት አቅጣጫና እየቆየም የፓርቲዎቹ ሥርዓት እየሆነ የመጣው ነገር ስለ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እያወሩ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆዎች በዋናነት ከላይ ከተመለከቱት በተቃራኒ መጓዝን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የማጋፈር ፖለቲካ ይባላል፡፡

በመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆ ፓርቲዎች በጋራ ሊገነዘቡት የሚገባ የሥነምግባር ደንብ ቢኖራቸው በሳይንስም የሚደገፍና ሥርዓቱን የገነቡ ሃገራትም ተሞክሮ የሚያረጋግጠው ነው፡፡ በትብብር መስራትና ልዩነትን አቻችሎ መጓዝና ለአብላጨው ተገዝቶ ወይም የህዝብን ፍላጎት አስቀድሞ ወደ መሃል መምጣትና በጋራ መስራትም የሚገባ እና የሚደገፍ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን በምርጫ 97 ወቅት በዚህ መስመርና ‹‹ህዝቡን ባነቃና ታሳቢ ባደረገው መልኩ መጥተው የነበሩ ፓርቲዎች በስተኋላ ወደ አንድነት የመጡበት መንገድ በራሱ ጸረ ዲሞክራሲያዊና ለዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በመገዛት

ሳይሆን ለግል ፍላጎት ነበርና ሲያልቅ እንዳያምር ሆኖ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ይልቁንም በጸረ ዲሞክራሲያዊ መንገድ መቋጨቱ ሳያንስ ወደ አንድነት ተሰብስበው የነበሩት ሁሉ ፖለቲካውንም ቀርቶ ባህላችንንም በማይመጥን መንገድ በዘለፋ እና በሽኩቻ መፈረካከሳቸውም አይዘነጋም፡፡ ከሁሉ የሚያስገርመውና ህዝብ እንደ ህዝብ ሳይሆን እንደሆነ ለመናገር የሚቀፍ መጠሪያ ተቀጥሮ ዛሬም ቢያንስ ሰዎቹ እንኳ ሳይለወጡ የማጋፈር ፖቲካ እየተደነሰበት መሆኑ ነው፡፡

እነዚያው ጀምረው ሲጨርሱ ያላማረባቸው ፓርቲዎች እስከነ ሰዎቻቸው ዛሬም ድረስ ስለጥምርትና ትብብር ያወሩና መሽቶ እስኪነጋ አንድነታቸውን አንኮታኩተው ይገኛሉ፡፡ ከዚያም የኢህአዴግ እጅ አለበት ሲሉም ያላዝናሉ፡፡ ማላዘናቸውም ባልከፋ፤ በየጥጋጥጉ የኢህአዴግ እጅ አለመሆኑን እርስ በእርሳቸው በሚወራወሩት ጦር መልሰው ያረጋግጣሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ አስቀድሞም ጨዋታው ዴሞክራሲያዊ ሳይሆን ግላዊ ስለሆነ እና በስም እንጂ ከላይ የተመለከቱት የመርህ ጥያቄዎች ቢያንስ በቤታቸው እንኳ መልስ ባለማግኘታቸው እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡

እንደ ትርፍ ጊዜ ሳይሆን እንደ ቋሚ ስራ ሊሰራ የሚገባው ፖለቲካ ለምርጫ ዋዜማ መሆኑ በራሱ የማያጠግብ እንጀራውን ብሂል ያስታውሳልና፤መደምደሚያው ምን እንደሚሆን ቢጠበቅም ቢያንስ ግን በዚህ በዋዜማው እንኳን አንዴ 33 አንዴም 9 አንዳንዴም መድረክና ሌላ ጊዜም መኢአድ ወአንድነት እያሉ ለመዋሃድ ያደረጓቸውን ጥረቶች የቋጩበት መንገድ የሚያበግን ነው፡፡

እናስ?ነው ጉዳዩ፤ እያንዳንዱ ፓርቲ አንዱ ከአንዱ ጋር ለመዋሃድ ቀድሞ ነገር ሲመጣ የራሱን ጠቀሜታ ታሳቢ ባደረገ ጸረ ዲሞክራሲያዊ አግባብ ነበርና የሚጠበቀውም ስለ ራሱ ጥቅም ድርድር የሚገባ መሆኑ የተለመደ ነውና ልዩነቶች ሁሉ በሁከትና በትርምስ ተጉዘው በ"ኢህአዴግ አፈረሰን" ሲቋጩ ማየት የተለመደ የለት ተለት ተግባር ቢሆን አይገርመንም፡፡

ያም ሆኖ ግን አማራጭ ፕሮግራም የሌላቸው መሆኑም ሲነቃ ከእርስ በእርስ ሽኩቻዎች ገና ያልተላቀቁና የውስጠ ዲሞክራያዊ ተስቦ ወረርሺኝ መላቀቅ ያቃታቸው መሆኑ፤ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ያልጨረሱትና ይልቁንም ያልጀመሩት የራሳቸው ፖለቲካ መኖሩ

ከ"ኢህአዴግ አፈረሰን" ጫጫታ በህዝብ ዘንድ ጎልቶ መታየቱ የትም የማያደርሳቸው መሆኑን የተገነዘቡት ፓርቲዎች ከ97 እንደ መማር የ97ቱን የማጋፈር ፖለቲካ መንገድ መርጠው መገኘታቸውም የሚያበግንና ይልቁንም ለራሳቸው ያላቸውን ወረደ ግምት የሚያመላክት ነው፡፡

አንደኛው ይነሳና ህግንና ህገ ወጥነትን ያጣቀሰ ማጥ ውስጥ ይዘፈቃል፡፡ ጉዳዩ የሚመለከተውና ሃላፊነት የተሰጠው የመንግስት አካልም ግና አስቀድሞ ለሚሰጠው ማስጠንቀቂያ (ሌላውና ግን ደግሞ እንዋሃድ ሲለው እምቢኛ እንደማለት ብሎ ሲያዝረጠርጠው የነበረው ሊሆን ይችላል ) ትክክል አይደለም ሲል እና በወረዱና ወስላታ በሆኑ ቋንቋዎች መግለጫ ይሰጣል፡፡ያኛውም አጋፋሪ እንዳለው ወይም እንደሚመጣ ያውቃልና ሲጋፈር ወደበለጠው ህገወጥነቱ ይሰጥማል፡፡ ከዚያም ያው የሚመለከተውና ህግን የማስከበር ሃላፊነት የተሰጠው አካል ወደ እርምጃ ሲገባ የማጋፈር ፖለቲካ ሰለባዎች ሁሉ በመግለጫ  ዜና እና በየማህበራዊ ሚዲያው ይንጫጫል። የድረሱልንም ጥሪ በማሰማት ዋና ስራው ከነበረው ፖለቲካ ወጥቶ ጊዜውን ይገዛል፡፡

ሰሞኑንም እያየነው ያለው ይህንኑ ነው፡፡ አንድነት ከተሰኘው ፓርቲ ተፈንክቶ ሰማያዊን የመሰረተው አካል በአንድነት ለቀረበለት የእንዋሃድ የቅርብ ጊዜ ጥያቄ እምቢኝ ማለቱንና ስለ እምቢኝ ባይነቱም የሰጠውን ምክንያት እናስታውሳለን፡  ፖለቲካ በትብብር አይመራም ሲል የነበረውና ትብብርም ካስፈለገ አንድነት አይመጥንም ሲል (እራሱን ለመካብም ሆነ የኪራይ ሰብሳቢነት ፍላጎቱን ለማርካት እንቅፋት ይሆነኛል በሚል እሳቤ አንድነቱን ቢያንኳስስም ግን ደግሞ ትክክል የሆነውን የአንድነትን ኪራይ ሰብሳቢነት በማውጣት) የነበረው ሰማያዊ ለራሱና ከላይ በተመለከተው ኪራይ ስብሳቢነት ፍላጎቱ ይሆኑኛል ያላቸውን 8 ፓርቲዎች መርጦ እራሱ ዋና አጋፋሪ የሆነበትንም አግባብ ሰሞነኛ ስለሆነ አንዘነጋም፡፡ ያም ሆኖ ግን በመሰረቱ ህገወጥ የሆነው ትብብር እና ህጋዊውን መንገድ ተከትሎ ትብበሩን ያላጸናው (ሆን ብሎ ነው) የፓርተዎች ትብብር ህገወጥ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ልማትን ለማደናቀፍና ህገወጥነቱን የበለጠ ገልጦ እርምጃን በመሻት፤ በሌላ አነጋገር ከመንጫጫት ለሚገኝ ጀብደኛ ፖለቲካ ብሎ ለጠራው ሰልፍ ህግ ነውና ዲሞክራሲያዊ መርሆውም ለህግ የበላይነት ቅድሚያውን ይሰጣልና ህጋዊ እርምጃ ሲወሰድ በመጀመሪያ የማጋፈር ፖቲካው መሰመር ላይ ተገኝቶ መግለጫ የሰጠው አንድነት ነው፡፡አንድነትና ሰማያዊ ፣ ሰማያዊ እና አንድነት  ፤ መኢአድና መድረክ፤ መድረክ

ከወዘተርፌዎቹ ጋር ምንና ምን እንደሆኑና ምንና ምን እየተሳሰቡ እንደሆነ በሚገባ የምናውቀው ዜጎች በብዛት ባለንበት ሃገር አንዳቸው ለአንዳቸው አጋፋሪ ሆነው መቅረባቸው በራሱ (እርምጃው ተገቢ አንኳ ባይሆን ) ጸረ ዲሞክራሲያዊና የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካ መሆኑን ማጤን መቼም የሚጋነን አይሆንም ፡፡ ይህን የማጋፈር ፖለቲካ እና የማጋፈር ፖለቲካው ተዋንያን እነማን እንደሆኑ ለማጠየቅና አሁንም ያለው ያውና የተለመደው መሆኑን ለመግለጥ ወደ ኋላ ተመልሰን ከምርጫ 97 እና 2002 ማስታወስ ግድ ይለናል፡፡

በሶስተኛው አገራዊ ምርጫ ፉክክሩ የድምጽ መስጠትና የቆጠራ ሂደቱ ሁሉ በሰላም መጠናቀቁን ተከትሎ አሸናፊው ወገን ቢለይም ተቃዋሚ ኃይል ይህን ውጤት በጸጋ ለመቀበል ያልፈቀደ የነበረ መሆኑ አይዘነጋም፡፡ የተቃዋሚው ኃይል መሪዎች ሳያሸንፉ አሸንፈናል ማለታቸው ሰሳያንስ ህዝቡ ከሰጣቸው ድምጽ በላይ በየእለቱ አዳዲስ ቁጥር እየፈበረኩ አሸነፍን የሚሉበትን መጠን በተለዋዋጭ አሃዝ ሲገልጹት የነበረ መሆኑም ይታወሳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የፓርላማ አብላጫ ወንበር መያዛቸውን የሚያረጋግጥላቸውን ቁጥር ይፈልጉና በህጋዊነት ካገኙት ቁጥር ጋር ያለውን ልዩነት አስልተው በዚህ ያክል የምርጫ ክልሎች የማጭበርበር ስራ ተሰርቷል ሲሉም እንደነበር በተለይ በኢሃድግ በኩል ዋነኛው የምርጫ አጋፋሪ የነበሩት አቶ በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫ ወጋቸው በሚገባ አውግተውናል፡፡  ይህን የለየለት የዜሮ ድምር ፖለቲካ በተለየ የሚስታውሱን ባለወግ እንደሚሉት ከሆነ ፦

ተቃዋሚዎች ይህን አቋም የማራመዳቸው እብደት ያነሰ ይመስል የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን በእሳት ላይ ነዳጅ ማርከፍከፍ መጀመሩ ደግሞ የተቃዋሚውን ጎራ እብደት ይበልጥ እንዲጠና አደረገው፡፡ የታዛቢ ቡድኑ ቀደም ሲል ተቃዋሚዎች ያነሱትን ተበደልን የሚል የሀሰት ውንጀላ  ሲያስተጋባ ከቆየ በኋላ የምርጫው ውጤት በተገለጸ ማግስት በተለይም ከግንቦት 20 በፊት በነበሩት ቀናት የምርጫ ትዝብቴ ነው በማለት ያዘጋጀውን ሪፖርት ለተቃዋሚዎች አሾልኮ ሰጣቸው፡፡ ወ/ሮ አና ጎሜዝ  ከአቶ ከማል በድሪ ጋር የተጻጻፉትን ደብዳቤ በየጋዜጣው ሲበትኑ መሰንበታቸው ሳያንስ ተቃዋሚዎች በምርጫው አሸንፈዋል የሚል ይዘት የነበረውን ሪፖርት ለመንግስት ከመስጠታቸው በፊት ለተቃዋሚዎች አቀበሏቸው፡፡

ሪፖርቱ በውክልናቸውና በተፈራረሙበት ግዴታ መሰረት ያዩትንና ያጣሩትን ነገር ብቻ መያዝ ሲገባው ወይዘሮዋ ሚዛናዊ ይሆናል ባሉት መሰረት ስልጣንን ሚዛናዊ በሆነ ልኬታ ለማከፋፈል የሚከጅል ነው፡፡ በምድረ ኢትዮጵያ ቀለም አብዮት ለማቀጣጠል ቆርጦ የተነሳው የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን ይህን ለማድረግ አንዳችም ይሉኝታ አልታየበትም፡፡ በተያያዙት አመጽ ቅኝት መስከን የተሳናቸው ተቃዋሚዎች እንደጌታ በሚሰግዱላቸው ፈረንጆች አሸናፊዎች ናችሁ መባልን ሲሰሙ ስልጣንን በጎዳና ላይ ነውጥ ለመንጠቅ ይበልጥ ተወራጩ፡፡ሲሉ በሚገባ ያስታውሱናል።ይህንና የኢሃዴጉ ዋና የምርጫ አጋፋሪ ትውስታ የምንቀበለው ዝን ብለን አይደለም።የቅንጅቱም አጋፋሪ የነበሩት  አቶ ገብረክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ በመጽሃፋቸው ገጽ 64 ላይ ይህንኑ ሃቅ እንዲህ ሲሉ ስላረጋገጡልን ነው። ‹‹ያም ሆነ ይህ ከ127 /አንድ መቶ ሃያ ሰባት/ በላይ የምርጫ ክልሎች ለኢህአዴግ በነጻ የተተወ እንደነበር የምርጫ ሰነዶች ህያው ምስክሮች ናቸው፡፡ በዚህም ስሌት በምርጫ ማጣሪያው ወቅት ድምጽ ተጭበርብሮባቸዋል የተባሉት 299 የምርጫ ክልሎች መሆናቸው እንዴት ታወቀ ?መንስኤው ምንድነው ? ወደፊት የምናየው ይሆናል ›› ካሉ በኋላ ገጽ 150 ላይ ደግሞ ‹‹ በምርጫ ቦርድ ታምኖበት የወጣው የይፋ ሪፖርት መሰረት ኢህአዴግ የነበረው የፓርላማ መቀመጫ ‹ያሸነፈው ደምጽ) 299 እንደነበር ያመላክታል፡፡ ተጭበርብሯል የተባለውም ይህንኑ ያህል ድምጽ እንደነበር ሲታወስ በእርግጥ አስተማማኝነቱ ሊያጠራጥር አይችልም ይሆን?" በማለት አሸንፈናል ተብሎ የተሰጠው መግለጫ መሰረት የሌለው እንደሆነ ቢያንስ በጥርጣሬ መልክ በመጽሃፋቸው የገለጹት ቢሆንም የቅንጅት መሪዎች በመላ ኢትዮጵያ በሁሉም የምርጫ ክልሎች አሸንፈናል ወደ ማለት ተሸጋገሩ፡፡ የዓለም የቀለም አብዮተኞችና የአገራችን ተቃዋሚዎች እጅና ጓንት ሆነው በሰላም የተጀመረውንና መቋጨት የሚችለውን ምርጫ ወደ ማፍረስ ያመሩት በዚህና ከላይ በተመለከተው  አኳኋን እንደነበር ማስታወስ የሰሞንኛውን የማጋፈር ፖለቲካ በቅጡ ለመገንዘበ ይረዳናል፡፡

የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ በምርጫው  አፈጻጸም ሆነ በተገኘው ውጤት ቅሬታ የተሰማው ወገን በመጀመሪያ ወደ ምርጫ ቦርድ ሂዶ አቤት እንዲል በቂ መንገድ የከፈተ መሆኑ ግልፅና የማያጠራጥር ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ካለ እንደገና ወደ ፍርድ ቤት ሂዶ እንዲያመለክት ሌለ ተጨማሪ መፍትሂ ደነገገ መሆኑም

እሙን ነው፡፡በህጋዊ መንገድ ተሟግቶ ለመርታትም የሚያስችል ህግ አክባሪነትና ዴሞክራሲያዊ መንፈስ ያልተለየው ዜጋ በዚህ ህጋዊ ስርዓት ሊመራ ግድ ይለዋል፡፡ ከዚህ የወጣውን ህገወጥና የጉልበት መንገድ ሊጓዝበት አይፈልግም፡፡ እነርሱ ግን እነዚህን ህጋዊ መንገዶች መከተል ያኔም ቢሆን ያልፈለጉ ነየነበሩ መሆናቸውን መገንዘብ አይከብድም ፡፡ ምርጫ ቦርዱንና ፍርድ ቤቶችን ለኢህአዴግ ያደላሉ ብለው በማጥላላት ስልጣንን በህገወጡ የጎዳና ላይ ነውጥ አማካይነት ለመረከብ የቋመጡበትን የዜሮ ድምር ጨዋታ ዛሬም ለመድገም እየታተሩ መሆኑን ልብ ይሏል ፡፡

ጉዳያችንንም የበለጠ ለማጠንከር ሌላ ትውስታም እናምጣ ፦ ዛሬም ያንኑ ታሪክ በመድገም ላይ የሚገኙት ሚዲያዎች በ97 ምርጫም ሆነ በ2002ቱ ምርጫ በኢትዮጵያ ትንሽ  ቀውስ በተፈጠረ ቁጥር ይህንኑ በከፍተኛ ቅብብሎሽ ማስተጋባት ይወዳሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ተሰሚነታቸው ከቀውስ ጋር ተያይዞ ወደላይ የሚወጣ በኢትዮጵያ የሰከነና የተረጋጋ ሁኔታ ሲኖር ደግሞ ሰሚ የሌላቸው ሚዲያዎች በመሆናቸው ነው፡፡  አቶ በረከትም ወቅቱን እንዲህ ሲሉ ያስታውሳሉ፦

አና ጎሜዝ ወደ ቢሮዬ መጥተው አውሮፓ ህብረት የታዛቢ ቡድን ሪፖርቱን አዘጋጅቶ መጨረሱንና በፍጥነት እንደሚያሰራጨው ገልጸውልኝ ነበር፡፡ ይህንኑ መነሻ በማድረግ አና ጎሜዝ ምን አይነት ሪፖርት እንዳዘጋጁ ስጠይቃቸው ሚዛናዊ /Balanced / ሪፖርት እንደሆነ ገልጸውልኝ ነበር፡፡ ሴትየዋ ለምን ተጨባጭ ሪፖርት /Objective/ ማዘጋጀትን ትተው ሚዛናዊ ሪፖርት ማዘጋጀት እንደመረጡ ስጠይቃቸው ደግሞ ‹‹በቃ ሚዛናዊ ሪፖርት ነው የማዘጋጀው › በማለት ድርቅ ያለ አመክንዮ አልባ መልስ ሰጡኝ፡፡

ተጨባጭ ሪፖርት የሚባለው ያየኸውን ሳትጨምር ሳትቀንስ የምትዘግብበት ሪፖርት ነው፡፡ በሌላ በኩል ሚዛናዊ ሪፖርት  የሚባለው ደግሞ ሪፖርቱን ያዘጋጀው አካል በህብረተሰቡ ውስጥ ካለው የተፋላሚዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣመና የሚደግፈውን ወገን ለመደገፍ የሚቃወመውንም ለመቃወም በማሰብ የራሱን አስተያየት ጨምሮ ቀንሶ የሚያዘጋጀው የየግል ስሜት የታከለበት ሪፖርት ነው፡፡ የምርጫ ታዛቢዎች ሁሉ እንዲታዘቡ ከሚጋብዟቸው መንግስታት ጋር የሚፈርሙት ስምምነት ተጨባጭ ሪፖርት ለማቅረብ ነው፡፡ የአውሮፓ ህብረት ከአገራችን መንግስት ጋር የተፈራረመውን ይህን

መሰሉን የአዘጋጆች ስሜት ያልተጫጫነው ተጨባጭ ሪፖርት ያቀርቡ ዘንድ ነው፡፡ ራሳቸው እንመራበታለን ብለው የሚያቀርቡት ስነ ምግባር መመሪያ የሚያዛቸው ተጨባጭ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ነው፡፡ የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ለመታዘብ ከመምጣታቸው በፊት ሪፖርታቸው በ ግለሰቦች ወይም በቡድኑ አባላት ስሜት የሚሞላ መሆኑ ቢታወቅ ኖሮም የሚጋበዙበት አንዳችም ምክንያት አልነበረም፡፡ ነግር ግን ሞያ በልብ ነው ብለው የመጡት ታዘቢዎች በይፋ የተፈራረሙበት ስምምነት ውጭ በመሄድ ሚዛናዊ ያሉትን ሪፖርት እንደሚገፉበት በድርቅና አሳወቁን፡፡

የቁጣ ወይም የስድብ ነገር ከተነሳ ተቃዋሚዎች በየኤምባሲው እየዞሩ ፈረንጆችን ሲማጸኑ የሚደርስባቸው ተግሳጽና ውርደት ሳይወሳ ቢታለፍ የምርጫ 97ን ታሪክ የተሟላ አያደርገውም፡፡ የአገራችን ተቃዋሚዎች እንደአብዛኛው በዲሞክራሲ ያልበለጸገ ህብረተሰብ ተቃዋሚ ከህዝብ ይልቅ በውጭ ቆንስላዎች ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚተማመኑ ናቸው፡፡ የህልውናቸው ምንጭ ህዝብ ሳይሆን ኤምባሲዎች እንደሆኑ አድርገውም ይቆጥራሉ፡፡ እውነትም ከእያንዳንዱ አባላቸው መዋጮ በመሰብሰብና ጠንካራ ድርጅታዊ ስራ በመስራት የህዝቡን አመኔታ አግኝተው ወደ ስልጣን ከመምጣት ይልቅ የሚቀናቸው ኤምባሲዎችን መወጣጫ አድርገው ወደ ስልጣን መምጣት ነው፡፡

እናም ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ እንዲህ ሆነ። አስቀድሞ በተቃደ እና "በታሰርን ተከለከልን "ከላይ የተመለከተው እና አስቀድሞ የተበላ መንገድ አስቀድሞ እውቅና የሌለው እውቅና ቢኖረውም ሆን ብሎ ልማት በሚካሄድበት ቦታ ላይ ሰላማዊ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ የቋመጠው ሰማያዊ ፓርቲ በህጋዊ አግባብ ህጋዊ እርምጃ ተሰጠው፡፡ የሚፈልገውም ይህን አይነት እርምጃ ነበርና ሌላው ተከትሎ ተንጫጫ፡፡ ሰማያዊ የፈለገው ሰልፍ ከነበረ መስቀል አደባባይን ለምን መሻት አስፈለገው? ሌላ አማራጭ ቢወሰድ አይችልም ነበር ወይ?፡፡ ዳሩ ግን ቢፈቀድለትም የሚወጣለት በጣት የሚቆጠር ህዝብ በባዶ መታበዩን ያጋልጠዋልና ክሽፈቱን እና ከክሽፈቱ የሚያገኘውን የማሳጣት ትርፍ አስቀድሞ አስልቶ የገባበት ነበር፡፡ ስለሆነም ኢሳት ልክ እንደ ምርጫ 97ቱ እና 2002ቱ ከላይ የተመለከተ ትውስታችን የግንቦት 2007ቱ ምርጫ ግንቦት 16 ድረስ መጓዝ ሳያስፈልገው ህዳር 27 ቀን ተጠናቋል የሚል መግለጫውን ሰጠ፡፡

ሰማያዊ ያወጣውን መግለጫ ተከትሎ ተንጫጭተው የነበሩ ፓርቲዎችም ሲሉ የነበረው "ተከለክልን ታፈንን" ከሰሞኑ ባደረጉት ህዝባዊ ስብሰባና ሰልፍ (ኤዴፓና መድረክ) ማን አፋኝና ማን ታፋኝ መሆኑን ያረጋገጡበት ሁኔታ መፈጠሩ የቅሌታቸውን ደረጃ የሚያመላክት ነው፡፡ ያም ሆኖ 100 ሺህ ሰው የጠበቀው መድረክ እራሱ በሰጠው መግለጫ 8 ሺህ መሆኑ የጩኸቱን ያህል ያልሆነውን ማንነቱን ያሳየ ሲሆን ፤ ኤዴፓም በመቀሌ ከተማ በሬዲዮ ማስታወቂያ ጭምር የታገዘ የቅስቀሳ ስራ ሰርቶ ህዝባዊ መድረኩን ስለማከናወኑ በሰጠው መግለጫ በማረጋገጡ የሰማያዊንም ሆነ እርሱን ተከትለው የተንጫጩትን ሁሉ ማንነት ያጋለጠ እና ድራማውም ከላይ የተመለከተው ትውስታችን ቀጣይ ክፍል መሆኑንም የበለጠ ማረጋገጥ የምንችለው የሰማያዊ ጩኸት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሌሎቹ ፓርቲዎች ሰልፍም ሆነ ስብሰባ ማድረጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በትውስታችን ላይ የተመለከቱት እና አብደውም ማሳበድ ስራቸው የሆኑት የሚዲያ ተቋማቶችና ሲቪል ማህበራት የሰጡት መግለጫን የተመለከትን እንደሆነ ነው፡፡

በምርጫ ታዛቢነት ገብተው ለፈረንጆች ፍርፋሪ ሲያድሩ በ97 ምርጫ የተገኙትና ለልፋታቸውም ማካካሻ የአፍሪካ ኃላፊነትን ከሰባዊ መብት አጠባበቅ ድርጅት ነኝ ባዩ ያገኙት አቶ ዳንኤል በቀለ ምርጫ 2007ን ጠብቀው ከሰማያዊ ፓርቲ ጩኸት ጋር አያይዘው ልክ እንደ 97ቱ "የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት አያያዝ አሳሳቢ ነው" ሲሉ ያው የተለመዱትንና ከላይ በትውስታችን የተመለከቱትን ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ፕሬሶች ያጣቀሱ ቃለ ምልልስ አብዶ ከሚያሳብደው የቪኦኤ ሬዲዮ ጋር አደረጉ፡፡ እነዚህ ሬዲዮኖች በዚህ ሳያበቁ የሰማያዊ ፓርቲን ጉዳይ ከግንቦት 7 ኢሳት ተቀብለው በሚገባ እና በፈለጉት መንገድ ይልቁንም ከላይ በተመለከተው ትውስታችን አግባብና ተመሳሳዩን መንገድ ተቀባበሉት፡፡ ቀጠሉናም በውጭ የሚገኙ እና በዜሮ ድምር ፖለቲካ የሚገኙት ከላይ በትውስታችን ላይ ባየናቸው ጉዳዮች ለይ ሁሉ እጃቸው የነበረበት ድረ-ገፆች ደግሞ ምርጫ 2007 ከወዲሁ የከሸፈ እንደሆነ ሟርታቸውን የመልቀቃቸው ምክንያት ከምርጫ የ97 እና 2002 አንጎበር አሁንም መንደሩ ባለመገላገሉ ነው፡፡ የዜሮው ድምር ፖለቲካ የሚጠይቀው ስትራቴጂም ህግና ህገ- ወጥነትን እያጣቀሱ መጓዝ በመሆኑ ነው፡፡

አውቀው በህገ ወጥ ድርጊት ውስጥ መንቦራጨቅና በዚህም ለሚደርሰው ጉዳት ገዢውን ፓርቲ ተጠያቂ ማድረግ፤ ተጠያቂነቱን ማራገብም የዜሮ ድምሩ ፖለቲካ መርህ ስለሆነም

ጭምር ነው፡፡ ባይሆንማ ኖሮ ህጋዊውን መንገድና ትክክለኛውን የፖለቲካ መስመር ለሚከተሉቱ አማራጭ ሀላፊነትና ህጋዊ ዋስትና የተሰጠ በመሆኑ ይህን ሁሉ ሳንሰማ አማራጭ ፕሮግራሞችን እንኮመኩም በነበረ፡፡ ነገር ዳግም አማራጭ የለምና ነገሩም በነበር ይቅርና ግና ጫጫታው የሚቀጥል እንደሆነ በመጠበቅ የመንጫጫታቸውን ሚስጥሮች ወቅታዊ ቁመና በሰማያዊ ፓርቲ ሰሞንኛ ፉከራና ከየአቅጣጫው ከሚገኙ የዜሮ ድምሩ ስብስብ አካላት ከሚሰጡ መግለጫዎች አንፃር በጥልቀትና በፖለቲካዊ ተጠየቆች መዝነን ማየት ይገባናልና ጉዳያችንን አንድ ክፍል በመጨመር ልናይ ግድ ይለናል ማለት ነው፡፡